**ቃለ ምልልስ ከአባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ጋር**

**የዚህ እትም እንግዳችን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅርብ ጊዜ ታሪክ ውስጥ እየታየ ላለው የስብከተ ወንጌል አገልግሎት መስፋፋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ በማበርከት ሰፊ ድርሻና ቦታ ያላቸው ፣ በወንጌል ትምህርት አሰጣጣቸው ብዙዎችን ከማትረፍ አልፈው እጅግ አድናቆትንና ተወዳጅነትን ያተረፉት፣ ስለዚህም «የዘመናችን ሐዋርያ» የሚል ቅጽል ስም የወጣላቸው ታላቅ አባት አባ ወልደ ትንሣኤ አያልነህ ናቸው።**
**አባ ወልደ ትንሣኤ በአሁኑ ጊዜ ነዋሪነታቸው በምድረ አሜሪካ ቢሆንም ሀገር ቤት በነበሩበት ወቅት በአዲስ አበባም ሆነ በተለያዩ ክፍላተ ሃገራት እየተዘዋወሩ ከፍተኛ አገልግሎት ማበርከታቸው የታወቀ ነው። እኚህ አባት ዛሬም የወንጌል አዝመራቸው በዓለም ዙሪያ ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ አፍርቶ ይታያል። አባ እየተዘዋወሩ ከሚያስተምሩት ምእመን ባሻገር በካሴት በተቀዱ ትምህርቶቻቸው የሚጽናናው ሕዝበ ክርስቲያን ቁጥሩ እጅግ የበዛ ነው። አባ ወልደ ትንሣኤ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ሃይማኖታቸውን ይበልጥ አውቀውና ተረድተው በፍቅርና በአንድነት ጸንተው እየኖሩ እምነታቸውን፣ ቋንቋቸውንና፣ ባሕላቸውን ጠብቃ ያቆየችላቸውን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናቸውን እንዲከተሉ፤ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ፣ ሳያሰልሱ ተጋድሎ በማድረግ ላይ የሚገኙ አባት ናቸው።**
**በአገልግሎታቸው ዙሪያ ስላጋጠሟቸው ፈተናዎችና ስኬታማ ውጤቶች እንዲሁም ስለ ወደፊት ራእያቸው ላደረግንላቸው ቃለ መጠይቅ እኚህ ታላቅ ሐዋርያ የሰጡንን መልስ ከዚህ ቀጥሎ እናቀርባለን።**

*1. **ከኢትዮጵያ ከወጡ ወዲህ ባለፉት** 13 **ዓመታት ውስጥ በኢትዮጵያና በመላው ዓለም በኦዲዮ እና በቪዲዮ በሚሰራጨው የትምህርት ካሴትዎ እና በተለያዩ ከተማዎች እየተዘዋወሩ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አብያት ክርስቲያን ምእመናንን በትጋት እያገለገሉ ሀዋርያዊ አገልግሎትዎን እየተወጡ እንደሆነ የታወቀ ነው። በአሁኑ ጊዜ የሚኖሩት የት ነው*?*

**መልስ፥**
**የምኖረው በሰሜን አሜሪካ በካሊፎርኒያ ግዛት በሎስ አንጀለስ ከተማ በድንግል ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ነው። ።በዋናነት የአገልግሎት ሥፍራዬን ሎስ አንጀለስ በማድረግ በካሊፎርኒያ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም የአሜሪካ ግዛቶች** ( **ስቴቶች** )**፣ በካናዳ፣ በአውሮፓ ቤተ ክርስቲያኔን በማገልገል ላይ እገኛለሁ።**

*2. **ወደ ሰሜን አሜሪካ ከመምጣትዎ በፊት በምን አገልግሎት ላይ ነበሩ*? ***የሚያገለግሉትስ የት ነበር*? ***ለአገልግሎትስ የሚያበቃ ትምህርት በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ የት ነበር የተከታተሉት*?*

**መልስ፥**
**በአገራችን በኢትዮጵያ በነበርኩበት ወቅተ ቤተ ክርስቲያንን አገለግል የነበረው፥በስብከተ ወንጌል አገልግሎት ነው። የአገልግሎት ቦታዬና ቋሚ ምድቤ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሆኖ በየክፍለ ሀገሩ በመዘዋወር ለቤተ ክርስቲያኔ የድርሻዬን አስተዋፅኦ ለማድረግ እሞክር ነበር። ትምህርቴን በተመለከተ በአገር ውስጥ በጎጃም፣ በጎንደር፣ በሸዋ ክፍለ ሀገር በዝዋይ በመሳሰሉት አቅሜ የሚችለውን የንባብ፣ የዜማ፣ የቅዳሴና የቅኔ እንዲሁም በአዲስ አበባ በቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት የአራት ዓመት የቴዎሎጂ ትምህርቴን ስከታተል በውጭ አገርም በአለሁበት በሰሜን አሜሪካ በካሊፎርኒያ የቋንቋ ትምህርቴን በኮሌጅ ደረጃ ለሁለት ዓመት የተከታተልኩ ሲሆን በኒው ዮርክ ግዛት በሚገኘው የቅዱስ ቭላድሚር የነገረ መለኮት ትምህርት ቤት** ST. VLADIMIR’S ORTHODOX THEOLOGICAL SEMINARY
**ለአንድ ዓመት የቴዎሎጂ ትምህርት ተከታትያለሁ። አሁንም ትምህርቴን የመቀጠሉ ሃሳብ እንዳለ ነው።**

*3. **በስብከት አገልግሎትዎ ላይ የሟቹን የብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስን ስም በተደጋጋሚ ሲያነሱ ይሰማሉ፤ እኚህ አባት በእርስዎ አገልግሎት ላይ የተለየ አስተዋጽኦ አላቸውን*?*

**መልስ፥**
**አዎ**! **ነፍሳቸውን ይማርና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጎርጎርዮስ በሕይወቴ ውስጥ የተለየ አስተዋጽኦ አላቸው። ምክንያቱም ዶግማና ቀኖናን እንዲሁም የአገር ልማድን ከዶግማና ከቀኖና ለይቼ እንድመለከት ያበቁኝ እርሳቸው ስለሆኑ ነው። በአጭሩ ለመተረክ፥ ያደግሁበትና ከልጅነት ጀምሮ በዲቁና አገልግሎት የነበርኩበት አካባቢ በክርስቶስ የደም ዋጋነት የቀረው የኦሪት ክፍል በአብዛኛው እንዳልቀረ የሚቆጥሩ ሰዎች ያሉበት**

ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ታቦቱን፣ እጣኑን፣ ሥዕሉን፣ ቅዳሴውን፣ ጸበሉን፣ ሰንበቴና ዝክሩን የመሳሰለ
ውን ሁሉ የሚቃወሙ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተቃዋሚዎች የበዙበት አካባቢ ነበር። በተለይም የአጽ
ዋማቱን ጊዜያት አስመልክቶ ማለትም ዓርብና ረቡዕን፣ ዐቢይ ጾምን፣ ጾመ ፍልሰታን በአጠቃላይ ሰባቱን
አጽዋማት በሙሉ እያንዳንዳቸውን በአዲስ ኪዳን ምዕራፍ እና ቁጥር ጠቅሼ እንዳስረዳቸው የሚጠይቁኝ
መናፍቃን ነበሩ። በተጨማሪም እነዚህን የጠቀስናቸውን ሁሉ ከክርስቶስ ደም ጋር አወዳድረን አንዳንድ ጊ
ዜም በክርስቶስ ደም ፈንታ ተክተን እንደምናመልካቸውና ትክክል እንዳልሆነ አድርገው ሊከራከሩኝ ሲሞ
ክሩ ትክክለኛውን ምላሽ ለመስጠት በቂ ትጥቅ አልነበረኝም። ከብፁዕ አቡነ ጎርጎሪዎስ ዘንድ ከተማርኩ በ
ኋላ ግን መልሱን አግኝቻለሁ። መልሱ ደግሞ በጣም አጭርና ቀላል ነበር። ምክንያቱም የኦርቶዶክስ ተዋ
ሕዶ እምነቴ የሚለው «ዓለም የዳነው ሰው በሆነው አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። ከእርሱ በቀር
ከዘለዓለም ሞት ያዳነን፣ ከዲያብሎስ ባርነት ነጻ ያወጣን ሌላ አዳኝ የለም።» ከላይ በዝርዝር የጠቀስና
ቸውና የመሳሰሉት በሙሉ ለእምነታችንና ለአዳነን አምላክ የፍቅር መግለጫ ሆነው በቀኖና ቤተ ክርስቲያ
ን መንፈስ ቅዱስ በሚመራቸው አባቶቻችን ያገኘናቸው የቤተ ክርስቲያን ሀብታት እንጂ የክርስቶስን ደም
የማይተኩ ለማዳን ሥራውም ጣውንት ያልሆኑ ናቸው። ይህንን ከእርሳቸው ስለተማርኩ ስማቸውን ደጋግ
ሜ አነሳለሁ።

*4. በቤተ ክህነት የስልጣን ተዋረድ ከፍተኛ ማዕረግ የሆነውን የሊቀ ካህንነት ስልጣንን ሲያገኙ የስብከተ ወ
ንጌል አገልግሎትዎን በይበልጥ በማስቀደም የሊቀ ካህንነቱን ስልጣን እንዲሁም አብሮት ሊመጣ የሚችለ
ውን ክብርና ጥቅም ይቅርብኝ ብለው በሰባኬ ወንጌልነት መቀጠልዎ ይሰማል። ይህ ምን ያህል እውነት ነ
ው? ለምን?*

<u>መልስ</u>፥
ነገሩ እውነት ነው የአራት ዓመቱን ኮርስ እንደጨረስኩ በአዲስ አበባ የቦሌ፣ የኮተቤና የየካ አውራጃዎች
ሊቀ ካህናት በመሆን ተመድቤ ነበር። ነገር ግን ይህ ሥራ ለእኔ ስጦታዬ ካለመሆኑም በላይ በደረጃም ከ
አቅሜ በላይ በመሆኑ ስጦታዬ የሆነውን ስብከተ ወንጌል አስቀድሜአለሁ። ክብርና ጥቅም ስለሚለው ግን
ከስብከተ ወንጌል የበለጠ የለም። ምክንያቱም ወንጌል እውነት ስለሆነች በወንጌል የተነሳ ከስም መጥፋት
ጀምሮ ብዙ መነቀፍን ያስከትላል። በወንጌል ምክንያት መነቀፍን የመሰለ ታላቅ ክብርም የለም። ሌላውን
መጥቀምና ሰማያዊ ክብር የሚገኘው በምድራዊ ውርደት ነውና።

*5. በስደት ሀገር የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንቅስቃሴ በአጠቃላይ ምን ይመስላል? አገር ው
ስጥ ከነበረው አገልግሎትዎ ጋር ሲያነጻጽሩት ምን ይመስላል?*

<u>መልስ</u>፥
መቼም እግዚአብሔር ለፈቀደለትና ለተሳካለት አገር ቤት እንዳለው የመሰለ አገልግሎት አይገኝም። ሆኖ
ም የምንኖረው እኛ በፈቀድነው ሳይሆን እግዚአብሔር በፈቀደው በመሆኑ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የ
ሆነው የውጭው አገልግሎትም እጅግ በጣም ጥሩ ነው። ሕዝቡ ዶግማና ቀኖናውን ለይቶ በመረዳት ይልቁ
ንም መልካም የሆነውን ሃይማኖታዊ ልማድ ከዶግማና ከቀኖና የተለየ መሆኑን እየተረዳና እያስረዳ በሃይ
ማኖቱ ሳይጠራጠር በቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎት እየተሳተፈ በእምነቱም ኮርቶ ለቀጣይ ትውልድ ለማስ
ተላለፍ እየጣረ ይገኛል። እኔም የአቅሜን እየጣርኩ እገኛለሁ።

*6. በሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ ሥር ተደራጅተናል የሚሉ አንዳንድ ወጣቶች ዶግማ እና ቀ
ኖና (እምነትና ሥርዓት) በሚለው ርዕስ ላይ ስላስተማሩት ትምህርት ተቃውሞአቸውን በአፍም፣ በበራሪ ወ
ረቀትና በመጽሔታቸው እያሰሙ ነው። ተቃውሞው ምንድን ነው? ትምህርቱስ ለቤተ ክርስቲያናችን አዲስ
ነውን?*

<u>መልስ</u>፥
ይህ በሰንበት ትምህርት ቤት ማደራጃ መምሪያ ሥር ነው የሚባለው ማኅበር ማኅበረ ቅዱሳን ነው። ማኅበ
ረ ቅዱሳንን እኔ አገር ቤት ሳለሁ የማውቀው አባቶችን አክባሪ ለሃይማኖቱ ተከራካሪ የመለያየትን ድልድ
ይ ሰባሪ ነው ብዬ ነበር። አሁን ግን በውጭ እንደማየው ማኅበሩን በሦስት ዓይነት መድቤ ለማየት ተገድ
ጃለሁ።
1ኛ. ሁሉን ነገር በመታገስና በማስተዋል በቅንነት የሚያገለግል ክፍል አለ
2ኛ. ባለማወቅ በስሜት ብቻ የሚነጉድ የሚሠራውን ማወቅ ያቃተው ክፍል አለ

3ኛ. የየትኛው ክፍል የጠላት እጅ እንደሆነ አይታወቅም ፍጹም ሰይጣን የሚጠቀምበት ክፍል ደግሞ አለ
። ምክንያቱም በዚህ ክፍል ልጆች በማያውቁት ነገር አባቶቻቸውን እንዲያዋርዱና አባቶችም በልጆቻቸው
እንዲያዝኑ እያደረጉ ነው። አባት ያዘነበት ልጅ ደግሞ ከነስሩ የሚነቀል ተክል እንደሚሆን አስተዋዮች
ይረዱታል።
የእኔን ትምህርት አስመልክቶም በተለይም ዶግማና ቀኖና የሚለውን ትምህርት እጅግ ሲቃወሙኝ ቆይተዋ
ል። በጣም የሚገርመው እነዚህ ሰዎች ሟቹን ብጹዕ አቡነ ጎርጎርዮስን ተቀዳሚና መሥራች አባት አድር
ገው ይቀበላሉ። ነገር ግን የደከሙበትን የዶግማና የቀኖናን ትምህርት ይቃወማሉ። ይህን ትምህርት እኔ የ
ተማርኩት ከእርሳቸው ነውና። ነገር ግን ይህን ትምህርት የሚቃወም የቪዲዮ ካሴት ለሕዝቡ በነፃ በማደል
ሕዝቡን ግራ እያጋቡ ይገኛሉ። «ትምህርቱ አዲስ ነው ወይ?» ለተባለው ግን አዲስ አይደለም። ዶግማ
ማለት እምነት ቀኖና ማለትም ሥርዓት ነውና። ደግሞም የቀኖና እና የዶግማ ትምህርት በጥራትና በጥንካ
ሬ ካልተሰጠ ኦርቶዶክሳውያን በተቃዋሚዎቻቸው ምክንያት እንደጠፍ ከብት እየተነዱ ወደ ማይጠቅማቸ
ው በመሄድ እነርሱነታቸውን እያጡ መሄዳቸው የማይቀር ነገር ነው።

*ለአንባቢዎቻችን ግልፅ እንዲሆንልን ለመሆኑ ዶግማ ማለት ምን ማለት ነው ቀኖናስ ?*

የቤተ ክርስቲያናችን መሠረታዊ አስተምህሮ ዶግማ እና ቀኖና በሚል በሁለት የተከፈለ ነው። ዶግማ ቃሉ
የግሪክ ሲሆን ትርጉሙ «እምነት» ማለት ነው። ዶግማ የእግዚአብሔርን መኖር፣ የእግዚአብሔርን አንድነ
ትና ሦስትነት፤ የክርስቶስን አዳኝነት የምንረዳበት ከእግዚአብሔር የተሰጠን ሰማያዊ ጸጋ ነው። ዶግማ የ
ሚሻሻል አይደለምና ጽድቅና ኩነኔ፥ ሞትና ሕይወት በዶግማ መሆኑን ተረድተን እስከ ሞት ድረስ መጠበቅ
አለብን። ይህንንም አስመልክቶ የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል እንዲህ ይላል «እስከ ሞት ድረስ የታመንህ
ሁን፣ የሕይወትንም አክሊል እሰጥሃለሁ»። በተጨማሪም በአዲስ ኪዳን ከተሻረው ከኦሪት ክፍል በቀር
በቅዱስ መጽሐፍ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃልም ከዶግማ ውስጥ መሆኑን ልናስተውል ይገባል።

ቀኖናም እንደዚሁ ቃሉ የግሪክ ሆኖ ትርጉሙ «ሥርዓት» ማለት ነው። ቀኖና በቅዱስ ሲኖዶስ የሚደነገግ
ሕገ ደንብ ወይም ሥርዓት ነው። የሚወሰነውም በዓለም አቀፍ ሲኖዶስና በሀገር አቀፍ ሲኖዶስ ነው። ከእ
ኛ ጋር አንድነት ያላቸው የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ያሉባቸው አምስት አገሮችን ያካተተ አንድ ዓ
ለም አቀፋዊ ሲኖዶስ አለ። ይኸውም የግብጽ፣ የአርመን፣ የሶርያ፣ የሕንድ እና የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲ
ያናትን ያጠቃልላል። በጋራ ስማቸው ኦሪየንታል አብያተ ክርስቲያናት ይባላሉ። እነዚህ አምስቱ አኃት አ
ብያተ ክርስቲያናት ዶግማቸው (እምነታቸው) አንድ ነው። በቀኖናም የሚያገናኛቸው ነገር አለ። በአገር አ
ቀፍ ቀኖና ቢለያዩም በሕብረት ማለትም በዓለም አቀፉ ቀኖና አንድ ናቸው። ለምሳሌ፥ የጋራ ቀኖና ከሚባ
ሉት መካከል አንዱን ብንጠቅስ ጳጳስ መሆን የሚችሉት ደናግል መነኮሳት ብቻ ናቸው። ከሚለያያቸው የ
አገር አቀፍ ቀኖና ለምሳሌ፥ እነሱ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገቡ ከነጫማቸው ይገባሉ። እኛ ወደ ቤተ ክርስ
ቲያን ስንገባ ጫማ አውልቀን እንገባለን። እነሱ በአንድ ካህን መቀደስ ሲችሉ እኛ ለቅዳሴ አምስት ካህና
ት መሆን አለብን።

እኛ ወደ ቤተ ክርስቲያን ጫማ አውልቀን የምንገባው የቤተ ክርስቲያናችን ቀኖና ስለሚያዝ ነው። እነርሱ
ግን ይህን የመሰለ ሥርዓት የላቸውም። እኛ ያለን ሥርዓት ይህ ብቻ አይደለም። ከኦሪት ጀምሮ የመጣ
ን ስለሆንን አሁን በሥርዓት መልክ የምንጠቀምባቸው ብዙ ነገሮች አሉ። ጫማ ማውለቃችንም ከዚያ ተ
ያይዞ የመጣ ሥርዓት ስላለን ነው።

*ስለዚህ አሁን ቤተ ክርስቲያንዋ ያላት ሥርዓት የኦሪትና የሐዲስ ጥምረት ነው ማለት ነው?*
<u>መልስ</u>
አዎ ከማለቴ በፊት ወንጌል በኦሪት ላይ ያላትን ስልጣን ለማስረዳት እፈልጋለሁ። ወንጌል በኦሪት ላይ
ሙሉ ስልጣን እንዳላት የሚጠቅሰውን የፍትሐ ነገሥት ክፍል ለመረጃ አቀርባለሁ። «በሥራ ፍጹም የሆነ
ው ሁሉ ጎዶሎውን ሊሽረው ይገባልና። ስለዚህም የጌታችን ሕግ [ወንጌል] ከእርስዋ የሚቀድመውን ኦሪት
ን ሻረችው። እርስዋ [ወንጌል] ግን መሻር አይገባትም። ከእርስዋ የሚበልጥ የለምና። እርስዋ የፍጹምነትና
የመጨረሻ ሕግ ናትና» ፍት. ነገ. መቅድም ገጽ 7። በተጨማሪም «ወአፈ ወርቅኒ ይቤ በእንተ ዝንቱ እ

ስመ እግዚአብሔር አብጠለ በዝንቱ ቃል [ወንጌል[ መብዝኅታ ለትእዛዘ ኦሪት» ትርጉም፥ «[ዮሐንስ] አፈ ወርቅም ስለዚህ ነገር እግዚአብሔር በዚህ ቃል [ወንጌል] ከኦሪት ትእዛዝ ብዙውን አሳለፈ ብሏል። (ፍት. ነገ አንቀጽ 23 ቁ. 804)። በዚህ መሠረት ወንጌል በኦሪት ላይ ሙሉ ስልጣን ስላላት ኦሪትን በአራት ከ ፍላ ታሳየናለች።

1ኛ. *<u>እንዳለ የተወሰደና በበለጠ ፍጹም የሆነ</u>*፥ ለምሳሌ አሥርቱ ትእዛዛተ ኦሪት እንዲሁም ከተሻረው ከ ኦሪት ክፍል በቀር በመጽሐፍ ቅዱስ ያለው የእግዚአብሔር ቃል በሙሉ የጸና ነው። «እኔ ሕግንና ነቢያት ን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ብሎአልና» (ማቴ 7፥17፤ ሉቃ 16፥17)

2ኛ. *<u>የተሻሻለው</u>*፥ ይኸውም ፍትሀ ኦሪት ወይንም የኦሪት ፍርድ ነው። ለምሳሌ፥
ሀ) «ማናቸውም ሰው አባቱን ወይንም እናቱን ቢሰድብ ፈጽሞ ይገደል» ዘሌ 20፥9
ለ) «ወንድም ሆነ ሴት በአመንዝራነት ቢገኙ ፈጽሞ እንዲገደሉ» ዘሌ 20፥11-21
ሐ) «አይን ለአይን፤ ጥርስ ለጥርስ፣ የገደለ ይሙት» የመሳሰለው ሁሉ የምሕረት ህግ በሆነች ወንጌል በን ስሀ እንዲመለሱ እንጅ እስከ ኃጢአታቸው እንዳይሞቱ በሚለው ተሻሽሎአል። ይህም በዮሐ 8፥3-11 በዝ ሙት የተከሰሰችውና ከጌታ ምህረት ያገኘች ሴት በቂ መረጃ ናት።

3ኛ. *<u>የተሻረው</u>*፥ በተፈጥሮ የረከሰ ወይም የተረገመ ነው የተባለው ሁሉ ድሮም ቢሆን በመጀመሪያ እግዚአ ብሔር ርኩስ ፍጥረት አልፈጠረምና አሁንም በአዲስ ኪዳን በክርስቶስ ደም ተሽሮአል። በ2ኛ ቆሮ 5፥17 እነሆ አሮጌው ነገር አልፎአል ሁሉም በክርስቶስ አዲስ ሆኖአል። ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረ ት ነው ይላልና። ለምሳሌ፥

ሀ) ያልተገረዘ ሰው የረከሰ ነበር። አሁን ግን ክርስቶስን አምኖ እስከተጠመቀ ድረስ ቢገረዝም ባይገረዝም ቦታ የለውም። ለመረጃ ያህል «እነሆ እኔ ጳውሎስ እላችኋለሁ ብትገረዙ ክርስቶስ ምንም አይጠቅማችሁ ም በክርስቶስ ኢየሱስ ሆኖ በፍቅር የሚሰራ እምነት እንጂ መገረዝ ወይንም አለመገረዝ አይጠቅምም። ገ ላ 5 ፥ 2-6፤ 1ቆሮ 7፥19

ለ) የሞተ ሰውና የእንስሳ በድን፥ (ዘኁ 19፥11፤ ዘሌ 11፥39) ይህን የሻረው የአዲስ ኪዳን ክፍል «ከአለማ ዊ ከመጀመሪያ ትምህርት (ከኦሪት) እርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ እንደ ሰው ወይም በኦሪት ሥር ዓትና ትምህርት፤ አትቅመስ፣ አትንካ፣ አትያዝ ትረክሳለህ ለሚሉ ትእዛዛት በኣለም እንደምትኖሩ ስለምን ትገዛላችሁ እነዚህ ሁሉ በመደረግ (መደረግን ለመተርጎም ነው በሀዲስ ኪዳን) ሊጠፉ ተወስነዋልና» ቆላ 2፥22
ሐ) ለምጽ ያለበት ሰው ሁሉ የረከሰ ነው ያባል ነበር። ዘሌ 13፥1-59 ቤትና ልብስ ሲበላሽም እንደለምጽ ይቆጠር ነበር። ዘሌ 14፥33-37። ይህ በማቴዎስ 26፥6-7 ባለው የወንጌል ቃል ተሽሮአል። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱ ቢታኒያ በለምጻሙ በስምኦን ቤት ተገኝቶአልና። በሰውነቱ ቁስልና ፈሳሽ ያለበት ሁሉ እ ንደረከሰ ይቆጠር ነበር። ዘሌ 15፥1-28

4ኛ. *<u>ፈጽሞ የተሻረ</u>*፥ መስዋእተ ኦሪት፣ ክህነት በዘር፣ በዮሐ 1፥29 ፣ ዕብ 7፥27 ፣ ዕብ 10፥3-14 ፈጽመው ተሽረዋል።

እና እኛ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ አማንያን የኦሪትም የአዲስ ኪዳንም ሰዎች ነን ስንል እነዚህን አራቱን ሳ ንዘነጋ መሆን አለበት። ይህ የቤተ ክርስቲያንዋ ትምህርት ነው።

***7. በመጽሔታቸው ላይ እንደሚነበበው እርስዎ በሚያስተምሩበት ወቅት «ሴት በግዳጅ ጊዜዋ ቤተ መቅደስ መግባት ትችላለች። እንዲሁም ምእመናኑን ያገኛችሁትን መብል ሁሉ ብሉ እንዲያውም አህያ፣ ቅማል፣ ውሻ፣ አሳማን ጨምሮ ብሉ» ብለው እንዳስተማሩ ነው። በእውነት ይህንን ነገር እርስዎ ብለዋል?***

***<u>መልስ</u>፥***

***ማኅበሩን ከሦስት በመመደብ አንደኛውን ሰይጣን የሚጠቀምበት ነው ያልኩት ለዚህ ነው። ምክንያቱም በ መጀመሪያ ውሸትን ከራሱ የፈጠረ «አቡሃ ለሐሰት» ወይም የሐሰት አባት ሰይጣን ነውና። ዋሽቶ የሚናገ***

ርና የሚጽፍም ከሰይጣን ነው። ለዚህ ነው ያላልኩትን ብሏል እያሉ የሚጽፉ። ፍትሐ መንፈሳዊ የቀኖና
መጽሐፉችን በንጽሕና ምክንያት የቤተ መቅደሱን ንጽሕና ለመጠበቅ ሲባል ሴቶች በወር አበባቸው ጊዜ
ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዳይገቡ ብሎ ወስኗል። የተወሰነውን ቀኖና ደግሞ ማሻሻል የሚችለው ቅዱስ ሲኖ
ዶስ እንጂ እኔ አይደለሁም። በርግጥ ቅዱስ ሲኖዶስ ከፈቀደ እኔም ትግባ ብዬ አስተምራለሁ። ከዚህ ው
ጭ ግን በስልጣኔ ትግባ ብዬ አላስተማርኩም። በእርግጥ «መርገም» «የመርገም ጊዜያት አትበሉ።» «በዚ
ህ ጊዜ ሴቷ እንደረከሰች አትቁጠሩ።» «መርገምና እርኩሰት በክርስቶስ ደም ተደምስሷልና፤ ክርስቲያን
ሴቶችም የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ በመሆናቸው መንፈስ ቅዱስ በሴቶች ልማድ ጊዜ ከእነርሱ አይለ
ይምና ርኩሰት አይባልም» የሚለው የዘወትር ትምህርቴ ነው። እጅግ የሚገርመው መርገሙ ከቀረ አሁን
ለምን ይከሰታል የሚሉም አሉ። መልሱ ግን አጭር ነው። ሙሴ ማንኛውንም ከሰው ልጆች የሚወጣን ፈ
ሳሽ ርኩሰት መርገም ብሎ በኦሪቱ ይጽፍ ስለነበር እንጅ የወር አበባ የመርገም ምልክት ሆኖ አይደለም።
ፍሬ የሚያፈሩ ዛፎች ከማፍራታቸው በፊት አበባ ማሳየት የተፈጥሮአቸው እንደሆነ ሁሉ የሴቶች ማሕጸ
ንም ሰውን ከማፍራቱ በፊት አበባን ማሳየት ከእግዚአብሔር የተሰጠ የተፈጥሮ ጸጋ ነውና እንደመርገም
ሊታይ አይገባም። አባቶቻችን ደስ በሚል ቋንቋ የወር አበባ ያሉትም ለዚህ ነው።

«ያገኛችሁትን ብሉ አለ» የሚሉትም ከተለመደው የውሸት ሀብታቸው ነው። ረሀብ ባለበት አገር ቢሆን እ
ንኳን በመሰለላቸው። አሜሪካን አገር የቆሻሻ መጣያ ሁሉ በሚተርፈው ምግብ ተሞልቶ ማን ምን ተቸግሮ
ነው ያገኛችሁትን ብሉ ብዬ የማስተምረው? በጣም የሚገርመው እኛ ባለንበት በሰሜን አሜሪካ ከአሳማ
በቀር አብዛኞቹን እኛ የማንበላቸውን እንስሳትና አእዋፍ አሜሪካኖችም አይበሉም። ይልቁንም አህያ፣ ው
ሻ፣ ፈረስ፣ የመሳሰለው የማይሞከር ነው። ታዲያ እኔ እንኳን ብሉ ብል እንኳን ኢትዮጵያውያን አሜሪካ
ኖች ይበሉልኛል? ደግሞስ «ቅማል ብሉ አለ» የሚሉት አሜሪካን አገር እንኳን የሚበላ የሚታይ ቅማል
አለ ወይ? አሳማን አስመልክቶ ግን በአጠቃላይ በውጭው ዓለም የተለመደ ምግብ በመሆኑ ኢትዮጵያውያ
ንን የሚጋብዙ ፈረንጆች አሳማ ሲያቀርቡላቸው ኢትዮጵያውያኑም አብዛኞቹ አንበላም ይላሉ። ለምን ሲ
ሏቸው በሃይማኖታችን ክልክል ነው በማለት አሳፋሪ መልስ ከመስጠታቸውም በላይ በፈረንጆች ዓለም የተ
ወለዱ ኢትዮጵያውያን ልጆቻቸውን ወላጆቻች የአሳማ ሥጋ ይከለክሏቸውና ለምን ሲሏቸው አሁንም በኦ
ርቶዶክስ ሃይማኖት የረከሰ ስለሆነ አይበላም ብለው በክርስቶስ ደም ጥላ ሆኖ ያለፈውን ዘሌዋውያን አስ
ራ አንድን በመጥቀስ የተዋህዶ ሃይማኖትን ባለማወቅ የሚያሰድቡ እየበዙ ስለመጡና ጥያቄውም አይኑን
አፍጥጦ ወደ እኔ ሲመጣ ክርስትና ሃይማኖታችን የሚለውን በወንጌል የተማርነውን በአደባባይ ሲጠየቅ በ
አደባባይ መልሻለሁ። መልሱም መብላቱን አትብሉ። ልጆችም እንዳይበሉ ከልክሉ። ነገር ግን ሃይማኖታ
ችን ይከለክላል አትበሉ። አሜሪካኖች በባህላቸው የማይበሉአቸው እንስሳት አእዋፍ እንዳሉ ሁሉ እኛም
አሳማንም ሆነ ሌሎችንም የማንበላው ባህላችን ስለሚከለክለንና ስለማንወድ ነው በሉ። ሃይማኖታችን ይ
ከለክላል ካላችሁ እናንተን እንደ እስላም እንደ አይሁድና እንደ ቡዲስት ነው የሚቆጥሯችሁ። ምክንያቱ
ም አሳማን መብላት ያረክሳል ኃጢአትም ነው ብለው የሚያምኑ ከላይ የጠቀስናቸው ክርስቲያን ያልሆኑት
እንጂ ክርስቲያኖች እንደዚህ ብለው አያምኑምና። ያውም በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ፈጽ
ሞ የማይሞከር ነው። ፍትሐ ነገስት አንቀጽ 23 «ቄሱ ወይም ኤጲስ ቆጶሱ ከመባልዕት ወገን ማንኛውንም
ያረክሳል አይበል» ይላል። የሸዋ ሊቀ ጳጳስ የነበሩት በብፁዕ አቡነ ጎርጎርዮስ የተጻፈው በቅዱስ ሲኖዶስ
ታርሞ የወጣው <u>*የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ*</u> የሚባለው መጽሐፍም በብሉይ ኪ
ዳን እንዳይበሉ የተከለከሉ እንስሳትና አዕዋፍ ዛሬም በአብዛኛው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ክርስቲያን ህዝብ
ዘንድ የማይበሉት የኦሪቱን ህግ የመጠበቅ ወይም ከዶግማም ሆነ ከቀኖና በመቁጠር ሳይሆን ሲወርድ ሲዋ
ረድ በመጣው የአገር ልማድ ብቻ እንደሆነ በግልጥ ያብራራል። ገጽ 16፣ 153 እና 154። በአዲስ ኪዳን
ም የሐዋ ሥራ 10፥9-16፣ ሮሜ 14፥1-4፣ ሮሜ 14-13-23፣ 1ኛ ቆሮ 10፥23-31፣ ቆላስይስ 2፥16፣ 1ኛ ጢሞ
4፥3-5፣ የመሳሰሉትን መመልከቱ ከበቂ በላይ ነው። እጅግ የሚገርመው በእኛ መርገም ምክንያት ምድር
ስትረገም ዘመኑም ዘመነ መርገም በመሆኑ በእዚያ የርኩሰት ዘመን ሙሴ አንዱን እንስሳ ርኩስ ሌላውንም
ርጉም እያለ ይጽፍ ነበር። ነገር ግን በደመ ክርስቶስ የሰው መርገም ሲደመሰስ በሰው ምክንያት የተረገመ
ች ምድርም ወደ ቀደመ ተፈጥሮዋ ተመልሳለች። ከደመ ክርስቶስ በኋላ ማንኛውንም ፍጥረት በተፈጥሮው
ያረክሳል ብሎ መናገርና የተረገመ ነው ብሎ ማስተማር እጅግ የክህደት ክህደት ነው። ይሁን እንጅ መር
ገመ ኦሪትን ወይም ዘሌዋውያን አሥራ አንድን ጠቅሶ የሚያስተምረው በማኅበረ ቅዱሳን ባለስልጣኖች ዘን
ድ አድናቆት ሲሰጠው እኔ ግን ባለማለቴ ወንጀለኛ ሆኜ በስም አጥፊነቱ ተወዳዳሪ በሌለው መጽሔታቸው

ያላልኩትን አለ በማለት ስሜን ለማጥፋት ይሞክራሉ። እግዚአብሔር ይመስገን ለእኔ ታላቅ ክብር ነው። ለእነርሱ ግን እጅግ መርገም ነውና እግዚአብሔር ይቅር ይበላቸው።

*8. አንዳንዶች ዶግማና ቀኖናን ለሕዝቡ ለማስተማር ጊዜው ገና ነው ብለው ይናገራሉ። እርስዎ ባሁኑ ጊዜ በዚህ ርእስ ለማስተማር ምን አነሳሳዎት፤ ለምንስ አስፈለገ?*

<u>መልስ</u>፥

የዶግማና የቀኖና ትምህርት ለእኛ ሕዝብ ጌዜው ገና ነው የሚሉ ሰዎች ጸረ ኦርቶኮክሶች ናቸው ምክንያቱም ትምህርቱ እንዲታወቅ አይፈልጉምና። ትምህርቱ ከታወቀ ኦርቶዶክሳውያን ለሚጠይቁት ሁሉ መልስ ስለሚኖራቸው ማንም አይነዳቸውም በአለት ላይ እንደተመሰረተው ቤት ነው የሚሆኑት። ለምሳሌ በሳምንት ሁለት ቀን ረቡዕ እና ዓርብን፣ ጾመ ፍልሰታንና የመሳሰሉትን አጽዋማት ጹሙ የሚል እስቲ ከመጽሐፍ ቅዱስ ወይም ከወንጌል አስረዳኝ ብሎ አንድ ተቃዋሚ ኦርቶዶክሱን ቢጠይቀው የሚመልሰውን መልስ ማወቅ አለበት። የኦርቶዶክሳዊው መልስ ጾም የእግዚአብሄር ትእዛዝ የሆነ ከእምነት የሚመደብ ሲሆን የጾም ጊዜያት ደግሞ በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰን ስርኣት ነው የሚል መሆን አለበት። አንድ ምእመን ይህንን መመለስ የሚችለው የዶግማንና የቀኖናን ትምህርት በሚገባ ከተማረ ብቻ ነው። ይህንን ለማስተማር ጊዜው ገና ነው ለተባለው፥ ክርስትናው አሁን ሁለት ሺህ ዓመት እየሆነው ነው። ክርስቶስ ዳግም እስኪመጣ መጠበቅ አለብን ማለት ነው? እኛ እኮ ከሰው በፊት ክርስትናን የተቀበልን ነን። ይህን ትምህርት ለመስጠት ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ቀርቶ አሁን ክርስትናን ለሚቀበሉ ሀገራት እንኳን ጊዜው ገና ነው አይባልም። በሌላ በኩልስ ከ12 ዓመት በፊት ኢትዮጵያ ሳለሁ ተምሬ አስተምረው የነበረ ትምህርት ነው። ምእመናንም ከመደሰት በቀር አንድም የከበደው ምእመን አጋጥሞኝ አያውቅም። አሁን ሲመሽ ያውም አስተሳሰብ ባደገበት ዘመን ያውም በሰሜን አሜሪካ ትንሽ የማህበረ ቅዱሳን አባላት በሰንበት ትምህርት ቤቶች ሰርጎ በመግባት ይህን የመሰለ ጠቃሚ ትምህርት በመቃወም እንቅልፍ ማጣታቸው ምስጢሩ ምን ይሆን? እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ የተሰወረውን እስኪገልጠው በትእግስት እንጠብቃለን።

*10. በቤተ ክርስቲያን ዙሪያ በሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚካሄደው በሐሰት የስም ማጥፋት ዘመቻ እንዲገታ መፍትሄው ምንድነው ይላሉ?*

<u>መልስ</u>፥

በቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ላይ የሚካሄደው የስም ማጥፋት ዘመቻ ወንጌሉን እንዳዳከመው በግልጥ ይታያል። በአባቶችና በማህበረ ቅዱሳን አባላት መካከል የአባትነትና የልጅነት ምልክት ሳይሆን የኖህና የካም ታሪክ የተደገመ ይመስላል። መፍትሄው «ለውሻ ከሮጡለት ለልጅ ካለቀሱለት» ነገር ይበላሻል እንዲሉ እነዚህን ልጆች አባቶች ሊቆጧቸው ሊገስጿቸውና አቅማቸውን እንዲያውቁ ሊቆጣጠሯቸው ይገባል። ለእነዚህ በስም ማጥፋት ተግባር ላይ ለተሰማሩ ሰዎች የልብ ልብ የሰጣቸው በቤተ ክርስቲያናችን አባቶች መካከል የተከሰተው የአስተዳደር ልዩነት ነው። እግዚአብሔር አምላክ በአባቶቻችን መካከል ፍቅርን ሰጥቶ ፍጹም አንድነትን እንዲያመጣልን የቤተ ክርስቲያኒቱ ልጆች ጸሎት መሆን አለበት።

*11. በመጨረሻውም ለኢትዮጵያውያን ወገኖችዎ የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ?*

<u>መልስ</u>፥

መልእክቴ በሃይማኖት በኩል ከምንጊዜውም በላይ ስለ ክርስትና እምነታችን ጠንቅቀን የምናውቅበት ጊዜ አሁን በመሆኑ እጅግ መትጋት አለብን። ይልቁንም ዶግማ ምን እንደሆነ፣ ቀኖና ስንልም ምን ማለታችን እንደሆነና በተለይም የሀገር ልማድን ከዶግማና ከቀኖና ለይተን በማወቅና በማሳወቅ ከአለት ላይ የተመሰረተውን ቤት ምሳሌነቱን እንተርጉመው። ከእንግዲህ እንደ ጠፍ ከብት ወደ ሌላ እምነት መነዳቱ ይቁም።

በማህበራዊ ኑሮአችን ደግሞ፥ «ነብር ዥንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያዊነቱን ሊለውጥ ይችላልን?» በማለት መጽሐፍ ቅዱሳችን በግልጥ አስቀምጦታል። ይህም ማለት ነብር በአካሉ ላይ የተለያየ ቀለም ቢኖረውም ነብሩ አንድ ነው። ኢትዮጵያውያንም ምንም እንኳን የተለያየ ጎንጎ፣ የተለያየ ባህል፣ የተለያየ ቀለም ቢኖራቸውም የኢትዮጵያዊነት አንድነታቸውን ሊለውጡ አይችሉም። ማለትም ቋንቋ፣ ጎሳ፣ ባህልና ቀለም የመሳሰሉት አንድነታቸውን የበለጠ ከሚያጠብቀውና ጌጥ ከሚሆናቸው በቀር ሊያናውጠው አይችልም ማለት ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ነብር ሲነኩት ቁጡ ነው። ኢትዮጵያውያንም አንድነታቸውን ሲነኩ

ባቸው እጅግ ቁጡዎች ለመሆናቸው አንዲት ሀገር አንዲት ኢትዮጵያን ከጀግኖች አባቶቻችን መረከባችን በቂ ምስክር ነው።

ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ! በዘር፣ በቋንቋ፣ በጎሳ፣ በባህልና በመሳሰለው እያመካኘ ሕዝብን የሚከፋፍል ፖለቲካ በቀጥታ ከዲያቢሎስ እንጂ ጤነኛ ከሆኑ ከሰው ልጆች አይደለምና አደራችሁን በሚያልፍ ፖለቲካ የማያልፈውን አንድነታችንን እንዳናጣ እጅግ ማስተዋል ያስፈልጋል። በእነዚህ ችግሮች ምክንያት መለያየቱ ማህበራዊ ኑሮን ብቻ ሳይሆን ቤተ ክርስቲያንንም የቱን ያክል እንደሚጎዳ ወንጌል ሲያስተምረን «እርስ በእርስ የምትለያይ መንግሥት ፈጥና ትጠፋለች» ብሎ ነው። መለያየት የሚጠቅመው ለዲያቢሎስ ብቻ ነው። የአሜሪካን ሀገር ሃምሳ ግዛቶች በአንድ ሕገ መንግሥት እና በአንድ ቋንቋ በመጓዛቸው እነሆ ዓለምን እየገዙ ይገኛሉ። ከእነርሱ የምንማረው ነገር አለ።

በተረፈ ግን አባት የሚወደውን ልጅ ይገስጻል ተብሎአልና በሀገራችን ላይ እየተከሰተ ያለውን የረሃብ፣ የበሽታና የመሳሰለውን ፈተና ሁሉ አባታዊ ተግሳጽ ሆኖልን እግዚአብሔርም በቃችሁም ብሎን ሀገራችንን ኢትዮጵያን ወደ ቀደመ ክብርዋ ይመልስልን። አሜን።